# 3ኛ የውጤት መስጫ ክፍለጊዜ ደረጃ/Grade K
# የወላጆች መመሪያ

ROCKVILLE, MARYLAND

በ3ኛ ማርክ መስጫ ወቅት፣ የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለፁት ፅንሰሃሳቦች እና ክሂሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።

እባክዎ ልብ ይበሉ፡- በ በኢታሊክስ የታዩት ጽንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ትምህርት ተሰጥቶባቸዋል ነገር ግን በሪፖርት ካርዱ ላይ ደረጃ/ዉጤት አልተገለጸም።

## ሒሳብ

### ጂኦሜትሪ

- በአካባቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን በቅርፆች ስም መግለፅ፣ እና የነዚህን ነገሮች አንፃራዊ ቦታዎች በላይ፣ በታች፣ በስተጎን፣ በፊት፣ በስተኋላ፣ እና አጠገብ የመሳሰሉ ቃላት በመጠቀም መግለፅ።
- ሁለት-እና ሦስት -እይታ አድማስ ቅርጾችን/three-dimensional shapes በተለያየ መጠን እና ቅኝቶች፣ ተመሣሣይነታቸውን፣ ልዩነቶቻቸውን፣ ክፍሎችን (ለምሳሌ፡- ጎኖች እና "ጥጎች" ስንት እንደሆኑ) እና ሌሎች ባሕርዮችን (ለምሣሌ፡- እኩል ርዝመት ያለው ጎን) ሥርአት ባልተከተለ ቋንቋ መተንተን እና ማነፃፀር።
- ከተለያዩ ነገሮች/ክፍሎች (ለምሣሌ፡- እንጨቶች እና ሸክላ ኳሶች) በዓለም ላይ ቅርጾችን ሞዴል ማድረግ እና ቅርጾችን መሣል።
- *ቀላል/ትናንሽ ቅርጾችን በመገጣጠም ትላልቅ ቅርጾችን መሥራት። ለምሣሌ፡- "እነዚህን ሁለት ባለ ሦስት ማዕዘኖች ሙሉውን ማዕዘን በመግጠም አራት ማዕዘን ቅርጽ መሥራት ትችላለህ/ትችያለሽ?"*

### ቁጥሮችና ግብረቶች በአስሮሽ ቤት

- በአንድ ቤት እና በአስር ቤት እስከ 100 መቁጠር።
- ስንት እንደሆኑ ለማወቅ ነገሮችን መቁጠር።
- ቁጠር/ሪ፣ ብዛትን መወከል፣ እና በእኩል ስብስቦች ማስቀመጥ።
- በታወቁ ማሰባሰብ ዉስጥ  የተቀመጡ ነገሮችን ሳትቆጥር/ሪ በቁጥር አሳይ።
- በሚታወቁ የስብስብ ዓይነቶች ውስጥ ያለውን ብዛት ለመወከል የአስርዮሽ ክፈፍ አወቃቀርን እንደ ሌላኛዉ መንገድ አድርጎ መጠቀም።
- እያንዳንዱ የተከታታይ/ቀጣይ ቁጥር ስም በቆጠሩ ቁጥር አንድ እየጨመረ የሚሄድን ብዛት እንደሚያመለክት ግንዛቤን መተግበር።

### ስሌቶች እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- *መደመርን እና መቀነስን በእቃዎች፣ በጣቶች፣ በአእምሮ ምሥሎች፣ በስዕሎች፣ በድምጾች፣ በትወና፣ በቃላት ማስረዳት፣ በአገላለጽ፣ ወይም የእኩል = ምልክት ወይም ተመጣጣኝ በማድረግ ማሳየት።*
- የመደመር እና የመቀነስ የቃላት ፕሮብሌሞችን ማቃለል፣ እና ፕሮብሌሙን ለመወከል እቃዎች ወይም ስእል በመጠቀም እስከ አስር መደመር እና መቀነስ።
- አስር ወይም ከአስር በታች  የሆኑ ቁጥሮችን በጣምራ/በጥንድ መለያየት/መነጣጠል.
  - o ከአንድ መንገድ በበለጠ በእቃዎች ወይም በስእል በመጠቀም፣
  - o እያንዳንዱን የተነጣጠሉ ቁጥሮችን በስእል ወይም በ እኩልነት(=) ጻፍ/ጻፊ (ለምሳሌ፡- 5 = 2 + 3 እና 5 = 4 + 1)።
- ከ 1 እስከ 9 ባሉ ማናቸውም ቁጥሮች ከአንድ የተሰጠ ቁጥር ጋር ሲደመር 10 የሚያመጣ ቁጥርን ፈልግ/ፈልጊ።
  - o ቁስ አካል ወይም ስዕሎችን በመጠቀም፣
  - o መልሱን በስዕል ወይም በቀመር ፃፍ(ፊ)።
- እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን በቅልጥፍና መደመር እና መቀነስ።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፡- ስነ ፅሁፍ

- የተለመዱ ታሪኮችን/ተረቶችን ፍንጭ በመጥቀስ እና ከድጋፍ ጋር እንደገና ተናገር(ሪ)።
- ከጽሑፍ ውስጥ ቁልፍ የሆኑ/ዋና ዝርዝሮችን እና ያልታወቁ ቃላትን ፍንጭ እና ድጋፍ እየሰጠህ(ሽ) ጥያቄዎችና መልሶችን አቅርብ(ቢ)።
- ገጸ-ባህርይን፣ ቅንብርን፣ እና ዋና ክውነቶችን ፍንጭ በማስያዝና በድጋፍ ለይ።
- በአቀራረብ በሥዕላዊ መግለጫ እና በታሪኩ መካከል ያለውን ግንኙነት ፍንጭ እና ድጋፍ በመስጠት አስረዳ(ጂ)።
- በምታውቀ(ቂ)ው ታሪክ ላይ የጀብዱ ተሞክሮ እና ገጠመኝ ልምዶችን ገፀ-ባህሪይ፣ፍንጭ እና ድጋፍ በመስጠት አወዳድር(ሪ)/አነፃጽር(ሪ)።
- በዓላማ እና በመረዳት ከባድ ጽሑፍን በቡድን የማንበብ ተግባር ላይ በንቃት ተሳተፍ/ፊ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፡- መረጃዊ

- በምንባቡ ውስጥ ስለ ቁልፍ ዝርዝሮች እና ያልታወቁ ቃሎች ፍንጭ እና ድጋፍ በመስጠት መጠየቅ እና ጥያቄ መመለስ።
- ዋናውን ርእስ በመለየት ቁልፍ የሆኑ ዝርዝሮችን ፍንጭ እና ድጋፍ በመስጠት ተናገር(ሪ)።
- የምንባብ ደራሲውን/ደራሲዋን እና በስእል የሚያብራራውን(የምታብራራውን) ስማቸውን በመጥቀስ እያንዳንዳቸው ስለሚያቀርቡት ሃሳብና ኢንፎርሜሽን ሚና ልዩነቱን ግለጽ/ግለጪ።
- በአቀራረብ በሥዕላዊ መግለጫ እና በታሪኩ መካከል ያለውን ግንኙነት ፍንጭ እና ድጋፍ በመስጠት አስረዳ(ጂ)።
- በዓላማ እና በመረዳት ከባድ ጽሑፍን በቡድን የማንበብ ተግባር ላይ በንቃት ተሳተፍ/ፊ።

### መሰረታዊ ክሂሎቶች

- *የህትመት ገጽታዎችን መረዳትክን/መረዳትሽን በተግባር አሳይ (ለምሣሌ፡- ቃላትን ከግራ ወደቀኝ፣ ከላይ ወደታች፣ እና ገጽ በ ገጽ፣ የላይኛውን እና የታችኛውን ፊደሎች መከተል)።*
- *የንግግር ቃሎችን፣ፊደላትን፣ እና የደብዳቤ -ድምፅ ግንኙነቶች መረዳትህ(ሽ)ን አሳይ።*

### ቋንቋ፡- የቃላት ዝርዝር ግኝትና አጠቃቀም

- ጽሑፍ ከፍ ባለ ድምፅ ሲነበብ እያዳመጥክ/ሽ እርዳታ ፍለጋ ጥያቄዎችን ጠይቅ/ቂ እና መልስ/ሺ፣ መረጃ/ኢንፎርሜሽን አግኝ/ኚ፣ ወይም ግልጽ ያልሆነን ነገር አስረዳ/ጂ።
- *በየረድፉ ያሉት ነገሮች የሚወክሏቸውን ጽንሰ-ሃሳብ ለማወቅ ተመሣሣይነት ያላቸውን ነገሮች/እቃዎች በረድፍ እየለየህ/ሽ ደርድር/ሪ።*
- ስለ ቁልፍ ዝርዝሮች ለጥያቄዎች መልስ በመስጠት ጮሆ ለተነበበ ፅሁፍ ግንዛቤ ማረጋገጥ።
- *በየጊዜው የሚነገሩ ግሦችን መረዳትህ(ሽ)ን ከተቃራኒዎቻቸው ጋር በማዛመድ አሳይ።*
- *ቃላት እና አጠቃቀማቸው በነባራዊ-ህይወት ያላቸውን ግንኙነት ለይ።*

### ተጨማሪ የምንባብ መረጃ

ተጨማሪ የምንባብ መረጃዎች ብቃት ያላቸዉን አንባቢዎች ለማዳበር/ለማጎልበት አስፈላጊ እና ጠቃሚ የሆኑ ክህሎቶችን ያካትታል። ሙአለ ህፃናት ከጨረሱ በኋላ፣ ተማሪዎች 44 ከፍተኛ ተደጋጋሚነት ያላቸዉ ቃላት እንደሚያነቡ ይጠበቃል። ተማሪዎች የላይኞቹን እና የታችኞቹን ፊደላት ስም እንዲሁም የመጀመሪያ ተነባቢ ድምፆችን አጣርተው እንዲያውቁና  እንዲጠሩ ይጠበቃል።

- ከፍተኛ የድግግሞሽ ቃላት (ከ 44 ውስጥ)
- *ፊደላትን መለየት ስማቸውን መጥራት-የላይኞቹ ፊደላት (ከ26 ውስጥ)*
- *ፊደላትን መለየት እና ስሞቻቸውን ማወቅ —የታችኞቹን ከ28 ውስጥ)፣ የተሽሞነሞነ/fancy (a) ን ይጨምራል a **እና** (g)g*
- *የመጀመርያዎቹ ተነባቢ ፊደላት/ኮንሶናንት ድምፆች (ከ19 ውስጥ)*

## ጽሑፍ

### የሃሳቦችና የአስተያየቶች አገላለጽ

- አንድ ነጠላ ክስተት ወይም ብዙ በልሉ የተያያዙ ሁነቶች/ድርጊቶችን ተርክ/ተርኪ።
- ስለ ሁነቶቹ/ድርጊቶቹ አፈፃፀም እንደ ክስተታቸዉ ቅደም ተከተል ግለጽ/ጭ እና ስለነበረው ሁኔታ ምላሽ ስጥ/ጭ።
- ትምህርት ሰጪ/ገላጭነት ያለው እና ስለተጻፈው ነገር ስም የሚጠቅሱ እና ስለተጻፈበት ርእስ መግለጫ የሚሰጥ ድርሰት ጻፍ/ጻፊ።
- ስለ ርእሱ ወይም ስለ መጽሐፉ ሃሳብ አስተያየት አመራረጥ (ለምሳሌ፡- እኔ የምመርጠው መጽሐፍ ...) ለአንባቢ አርእስቱን ወይም ስለሚጽፉት የመጽሐፍ ስም የሚገልጹበት ድርሰት ጻፍ/ፊ።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- ከጓደኞች ጋር መተባበርን ጨምሮ ጽሑፎችን ለመጻፍ እና ለማሳተም/ለማተም የተለያዩ ዲጂታል መሣሪያዎችን አሥስ(ሺ)።
- በጋራ ምርምር እና ጽሑፍ በሚደረግባቸው ፕሮጀክቶች ተሳተፍ/ፊ (ለምሳሌ፡- በምትወደ(ጂ)ው ደራሲ የተጻፉ መጻሕፍትን በመፈለግ ስለመጽሐፎቹ አስተያየት ግለጽ(ጪ)።
- ከልምድ/ገጠመኝ የተገኘ መረጃ በማስታወስ/በመጥቀስ ወይም ከተሰጡ

ምንጮች መረጃ በመሰብሰብ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት።
- ስለምታውቃቸው/ስለምታውቂያቸው ሰዎች፣ ቦታዎች፣ ወይም እቃዎች፣ ፍንጭ በመስጠት ከድጋፍ ጋር ግለጽ(ጪ)።
- በጋራ ቋንቋ እንቅስቃሴዎች ሙሉ አረፍተነገሮችን ማፍለቅ።
- ተጨማሪ ዝርዝር ለመስጠት እንደተፈለገዉ ምስሎችን/ስዕሎችን ወይም ሌላ የሚታዩ ነገሮችን ጨምር/ሪ።
- ከጓደኞች የሚሰነዘሩ ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን ለመመለስ ከመመሪያ ጋር ጽሑፍ ለማዳበር እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ዝርዝሮችን ጨምር(ሪ)።

### የቋንቋ አጠቃቀም

- ቀላል ቃላትን ፊደሎች በድምፅ መዘርዘር/Spell።
- ስዕላዊ መግለጫው ጋር ለማስማማት ቃላትን ወም አረፍተነገሮችን ጻፍ/ፊ።
- በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ስሞችን፣ ግሦችን፣ እና መስተዋድዶችን ተጠቀም/ሚ።
- የጥያቄ ቃላትን መረዳት እና መጠቀም።
- በአረፍተነገር ውስጥ ስምን እና እኔ "I" በሚለው ተውላጠ ስም ስርአተ ነጥብን በመጠቀም የመጀመሪያውን ፊደል በትልቅ ጻፍ/ፊ።

## ሳይንስ

### የህይወት ሳይንስ

- ህይወት ያላቸው ነገሮች በዓለም ላይ የትም እንደሚገኙ እና በተለያየ ሥፍራ የሚኖሩት የተለያዩ ዓይነት ህይወት ያላቸው ነገሮች መሆናቸውን ግንዛቤ ይኑርህ/ሽ።
- ሰዎች እንደ መጠን፣ ቅርጽ፣ ወ.ዘ.ተ ያሉ የተለያየ አይነት ውጫዊ ገጽታዎች እንዳላቸዉ፣ ኢንፎርሜሽን እና ቀጥተኛ ማስረጃ ሰብስብ/ቢ። ነገር ግን እነርሱ ከሌሎቹ እንስሣት ይልቅ እርስ በርሳቸው ይመሣሠላሉ።
- የእፅዋት እና የእንስሳት ውጫዊ ገፅታ በተለያዩ አካባቢዎች ለመኖር እንዲችሉ እንደሚረዳቸው እያነጻፀርክ(ሽ ) አስረዳ(ጂ)።
- እፅዋት እና እንስሣት የሚኖሩባቸውን የሚታወቁ ልዩ ልዩ ቦታዎች በመመርመር ስለ ስፍራው እና በዚያ ስለሚገኙት ህይወት ያላቸው ነገሮች ግለጽ/ጪ።
- የምታውቃቸውን የተለያዩ እንስሳት እና እጽዋትን በማስተዋል (ለምሳሌ፡- በት/ቤት ግቢ ውስጥ፣ በጎረቤት፣ እና በቤት አካባቢ) በመካከላቸው ያለውን የተመሣሳይነት እና የልዩነት ሁኔታዎችን አስተዉል(ይ)/አግኝ(ኚ)።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ስነ-ነዋይ/ኤኮኖሚክስ

- ገደብ በሌለው የኤኮኖሚ ፍላጎት ምክንያት ሰዎች ስለሚያደርጉት ምርጫ አስረዳ/ጂ።
- ግብአቶች/ሪሶርሶች ምርትን ለማምረት ጠቃሚ መሆናቸውን ለይተህ(ሽ) እወቅ።
- የአካባቢ ገበያዎችን ዓይነት ለይ።
- እቃዎች እንዴት እንደሚገኙ ግለጽ/ጪ።

## መረጃዊ/ኢንፎርሜሽናል ማንበብ እና መጻፍ

- በልብ ወለድ እና ልብ ወለድ ያልሆነ ስነጽሑፍ እና እውነተኛ ህይወት ውስጥ ያሉ ግንኙነቶችን መለየት።
- የተሰጠ/የተመደበ ወይም በግል የሚያስፈልግ መረጃ መለየት።
- መረጃዎች ለማግኘት በተለዩ ምንጮች መገልገል።
- ውሂብ/መረጃ በተለያየ ቅርፀት መቅረፅ/መመዝገብ።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።
- ለማጋራት የሚያስፈልጉትን መረጃ ግኝቶች/ እና ድምዳሜ ለማዘጋጀት የተለያዩ ቅርፀቶችን ይጠቀሙ።

## ስነጥበብ

### የሥነ ጥበብ ፈጠራ እና ከሥነ ጥበብ ጋር መገናኘት

- ለስነጥበብ ስራዎች ሀሳቦችን ለማፍለቅ በራስ-መር ፍለጋ/አሰሳ ውስጥ መሳተፍ።
- በስነ-ጥበብ ስራዎች ውስጥ ሐሳቦችን ለማስተላለፍ የሥነ-ጥበብ ክፍሎች እና ንድፍ መርሆዎች ይምረጡ እና ይጠቀሙ።
- ለስነጥበብ መስሪያ መሳሪያዎችን እና ሚዲያ ለመጠቀም የሚያስችሉ በርካታ መንገዶችን ፈልግ/ጊ።
- ጥሩ የሞተር አጠቃቀም ችሎታ ለማሳየት የስነጥበብ መሥሪያ መሣሪያዎችን በሙያዊ መንገድ ተጠቀም(ሚ)።
- ለምልከታ፣ ለማስታወስ፣ ወይም ለምናብ ምላሽ ስነጥበብ ፍጠር/ሪ።
- የሥነጥበብ ሥራን ዓላማ ለይተህ/ሽ እወቅ/ቂ።

### የኪነጥበብ አቀራረብ እና የኪነጥበብ ግብረመልስ

- ለእይታ የሚቀርብ የሥነጥበብ ሥራ መምረጥ እና ምርጫዉን ማረጋገጥ/ስለ ምርጫዉ ማሳመኛ ማቅረብ።
- በአንድ ቦታ ላይ ለእይታ የሚቀርብ የሥነጥበብ ሥራ አዘጋጅ(ጂ)።
- የሥነጥበብ ሥራን ለማየት ለምን ብዙ ቦታዎች እንዳሉ ምክንያቶችን ለይ።
- በሥነጥበብ ሥራ እና በአካባቢ የሚታዩ የስነጥበብ ውጤቶችን እና የንድፍ መርሆዎችን በመለየት ገለጽ(ጪ)።
- የሥነጥበብ ሥራዎችን ለመተርጎም ዝርዝሮችን እና ዋናዉ ቁም ነገርን/ጉዳዮችን መለየትና መግለፅ።
- አንድ የስነጥበብ ሥራ መርጠህ(ሽ) ለምን እንደመረጥክ(ሽ) ምክንያቱን ገለጽ/ጪ።

## ሙዚቃ

### ሙዚቃ ማንበብ

- ለስዕል ምስሎች ምላሽ ረዥም/አጭር እና ከፍተኛ/ዝቅተኛ ድምፆችን በመወከል ትክክለኛ ድምጾችን ፍጠር(ሪ)።

### የሙዚቃ ፈጠራ

- የእንስሳት እና የአካባቢ ድምፆችን የማስመሰል  ድምፅ ተጠቀም።

### የሙዚቃ ምላሽ/ዝንባሌ

- በሙዚቃ ውስጥ ስለሚደጋገሙ አንጓዎች ለይ።
- ድምፆችን እንደ ፈጣን/ዝግ ያለ፣ ጮክ/ለስላሳ፣ ረዥም/አጭር፣ ከፍ/ዝቅ ያሉ በማለት ለይ።
- በዜማ/በዝማሬ ጨዋታ ላይ ቀላል መመሪያዎችን ወይም የቃላት ምልክቶችን ተከተል/ይ
- በተለያዩ ሜትሮች በመወዛወዝ እና ያለውዝዋዜ ለሙዚቃ እንቅስቃሴ መልስ ስጥ/ስጪ።
- ስለሌሎች ትምህርቶች ፅንሰሐሳቦችን ለማጠናከር በመዘምር፣ እና በመንቀሳቀስ ሙዚቃ ተጫወት(ቺ)።

### ሙዚቃ መጫወት

- በተወሰነ የድምፅ ቅላፄ ዘምር/ሪ።
- የድምፅ ቅላጼን በተለያዩ መንገዶች የሚጠቀሙ ዜማዎችን ዘምር(ሪ)
- በክፍል ውስጥ መሣሪያዎች ስንኝ/ዜማ አወጣጥን በማስመሰል ተጫወት(ቺ)።
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚገኙ መሣሪያዎች በመጫወት የማያቋርጥ/ቋሚ ድምፅ/ምት ማሰስ/መፈለግ
- ዘምር/ዘምሪ፣ ተንቀሳቀስ/ተንቀሳቀሺ፣ እና ከት/ቤት እና ከማህበረሰብ ጋር የሚገናኝ ዓይነት ሙዚቃ ተጫወት/ተጫወቺ።
- የተለያዩ የዓለም ባህሎች ሙዚቃን ማዳመጥ እና መዘመር
- የዝማሬ ጨዋታዎችን እና የጣት ጫወታ በማዳመጥ እያተጫወትክ(ሽ)፣ በደረሷቸው/በፈጠሯቸው ሰዎች ህይወት ላይ የነበራቸውን ጥቅም እና ፋይዳ አስረዳ(ጂ)።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### ጤንነትን የሚያበለጽግ- አካላዊ ብቃትና እንቅስቃሴ

- የአካል እንቅስቃሴ በሰውነት ሥርዓት ላይ የሚኖረውን ውጤት ለይተህ(ሽ) አሳይ።
- እንቅስቃሴ ማድረግ ልብ ላይ ምን ውጤት እንዳለው ተናገር/ተናገሪ።
- የአካላዊ እንቅስቃሴ ጠቀሜታዎችን መርምር/ሪ።
- በስነ-ምግብ እና በአካላዊ እንቅስቃሴ መካከል ያለውን ግንኙነት ግንዛቤ ውሰድ/ጂ።
- አልሚነት ያለው/ለሰውነት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የያዙ ምግቦችን ለይ።

- የተለዩ የሰውነት ክፍሎችን የሚያንቀሳቅሱ ጡንቻዎችን ወይም የጡንቻ ቡድኖች ተገንዘብ/ቢ።

**የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች**

- እንቅስቃሴ በማድረግ ሚዛን የመጠበቅን ጽንሰሃሳብ ተለማመድ/ጂ።
- ስለ የማይለወጥ እና ስለ ተለዋዋጭ ሚዛን የመጠበቅን ጽንሰሃሳብ በእንቅስቃሴ ውስጥ አሳይ።
- ገንቢ አስተያየቶች ላይ በመመርኮዝ አፈጻጸምህ(ሽ)ን አሻሽል/ይ።
- ከአንድ የአካል ክፍሎች፣ዕቃዎች፣ እና/ወይም ሰዎች ጋር በተዛመደ እንቅስቃሴ ለማድረግ መለማመድ።
- አምስቱን አይነት ማስነሣት እና ማሳረፍ/take-off and landing ተለማመድ/ጂ።
- ፈጠራዊ የእንቅስቃሴ ክሂሎቶችን ማዳበር።
- የሰውነት/የአካል ክፍሎችን በተለያዩ ቅርጾች አንቀሳቅስ/ሺ (ቆልማማ/የታጠፈ፣ ጥምዝ፣ ጠባብ፣ እና ሰፊ)።
- ክብደትን ከተለያየ የአካል ክፍሎች ወደሌላ ማስተላለፍን ቃኝ/ኚ።

## የጤና ትምህርት

**ስነ-አመጋገብ እና የአካል ብቃት (NF)**

- በስሜት ህዋሳት እና በምግብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለይ።
- የተለያዩ ምግቦችን ምንጭ ተናገር/ሪ።
- ተገቢ የሆነ የአመጋገብ ስርአትን ግለጽ/ጪ።
- በምግብ  እና በጤና መካከል ያለውን ግንኙነት ግንዛቤ ውሰድ/ጂ።
- የምግብ ፈርጆችን ለይ።

**የቤተሰብ ህይወት እና ሰብአዊ ወሲባዊነት (FLHS)**

- ስለ ቤተሰብን ክፍል/ዩኒት አብራራ(ሪ)/ፍቺ ስጥ(ጪ)።